**ትንቢተ ዮናስ**

በሕዝቧ መካከል ዐመፅ ሰለ ጸና
በጣም ተቈጥቼ አዝኛለሁና፤
ይህንን ለነነዌ ንገራት ባዋጅ
አለና ለዮናስ ለአሚታይ ልጅ፤
እግዚአብሔር አዘዘው እንዲሄድ በቶሎ
ዮናስ እንቢተኛው አሰበ ኮብልሎ
ካምላክ ተደብቆ አምልጦ ሊጠፋ
ወደ ተርሴስ ሲጓዝ ሄደ ወደ ያፋ።
ዋጋ ከፈለና በመርከብ ተሳፍሮ፤
እያጕረመረመ ባሕሩን ተሻግሮ
ዮናስ ተደብቆ ሲሄድ በግሥገሣ
ከእግዚአብሔር ተልኮ ማዕበል ተነሣ
ታላቅ ሞገድ ሆነ ባሕሩ ተቈጣ
መርከበኞች ፈሩ ትልቅ ሽብር መጣ
መርከቡ እንዲቀልለው እናድርግ እያሉ
አንሥተው ብዙ ዕቃ ወደ ባሕር ጣሉ
ባሕሩ ባሰበት በጣም ተናወጠ
መርከቡ መሰለ የተገለበጠ
ሰው ሁሉ ተነሣ ጸሎት ለማድረስ
ይኸ ሁሉ ሲሆን ተኝቷል ዮናስ
ወደ ዮናስ ሄዶ የመርከብ አለቃ
ቀሰቀሰውና ከእንቅልፉ ሲነቃ
እግዜር እንዲያድነን ከዚህ ክፉ ጥፋት
ተነሥ ጸልይ አለው ይብቃህ ማንቀላፋት
በመርከብ ውስጥ ያሉ ሰዎች ተሰብስበው
ተመካከሩና በነገሩ አስበው
አለ ኃጢአት ሠርቶ ከእኛ ጋር የመጣ
ለይተን ለማወቅ እንጣጣል ዕጣ
አለዚያ አንድንም ስለ ተባባሉ
ተሰበሰቡና ዕጣ ቢጣጣሉ
እውነትም እንዳሉት አጥፊው ሰው ታወቀ
በእንቢተኛው ነቢይ በዮናሰ ወደቀ
ዮናሰ ተረዳና እጁ እንደ ተያዘ
ያጠፋውን ጥፋት ገልጦ ተናዘዘ
ምነው ባትመጣ ተጣልተህ ከጌታ
እየው መርከባችን እንደሚንገላታ
ቍጣው እንዲታገሥ ለማግኘት ጸጥታ
በል አንተው ፍረደን ምን ይበጃል ቢሉ
ዮናስ መለሰና እዚህ ያለ ሁሉ
ስለ ምን ይጠፋል በኔ የተነሣ
ወደ ባሕር ጣሉኝ አለብኝ አበሳ
ተመልከቱ እነሆ ሥራውን ዐወቀ
ጥፋቱን ገለጠ ይኸው መች ደበቀ
እሱው ከፈረደ መልሶ በራሱ
ምን እናድርግ ብለው ሊጥሉት ተነሡ
ከደሙ እንጻን ሲሉ ለእግዜር አመልክተው
ወደ ባሕር ጣሉት ዮናስን አውጥተው
በዮናስ ላይ ኖሮ የመጣው ይህ መዓት

ባሕሩ ጸጥ አለ ልክ በዚያው ሰዓት

**ምእራፍ ሁለት**

ዮናስም ተውጦ በእግዚአብሔር ፈቃድ
ሦስት ቀን ሦስት ሌት ሲያድር በሣ ሆድ
ተቀይመህ ኖሮ ከላይ ብትቈጣ
እንዲህ ያለ መዓት በራሴ ላይ መጣ
የባሕሩ ሞገድ እኔን አዋከበኝ
ውኃና ጨለማ ሲኦልም ከበበኝ
እያለ ባሣ ሆድ ዮናስ ሲቀመጥ
አምላኩን ለመነው በመለማመጥ
የታዛዥነትም ጣባይ እያሳየ
አዝኖ ተጸጽቶ ከልቡ ጸለየ
ምን ግዜም ቢቈጣ ነውና መሓሪ
ፊቱን መልሶለት ታረቀው ፈጣሪ
ዓሣውም ዮናስን ውጦ ሳያስቀረው
ከባሕር ተፋና መሬት ወረወረው

**ምዕራፍ ሦስት**

ይህንን የእኔን ቃል ስማና በቶሎ
ሄደህ ለነነዌ እንድተነግራት ብሎ
ደገመና እግዚአብሔር ዮናስን አዘዘ
ነነዌ ሊገባ ዮናስም ተጓዘ
ድምጡን ከፍ አድርጎ ነቢዩ ዮናስ
ከዛሬ ጀምሮ አርባ ቀን ድረስ
ነነዌ ጠፊ ነች ከሥር ተገልብጣ
አለና ለፈፈ የእግዚአብሔር ቍጣ
ሳያንገራግሩ ሁሉም ስላመኑ
የነነዌ ሰዎች ተጨንቀው አዘኑ
ከትልቅ ጀምሮ ሕፃኑ ድረስ
ሕይወቱ የቆመች በሥጋ በነፍስ
ሰውም ሆነ እንስሳ ይቀበል ንስሓ
ፍጡር ሁሉ ይጹም ይለይ ከእህል ወኃ
ሁሉም ከልብ አዝኖ ማቅ እየለበሰ
ከክፉ ወደ ደግ እየተመለሰ
መቼም ወሰን የለው የለው እግዚአብሔር ምሕረቱ
ይጸልይ አለና ይለምን በብርቱ
ንጉሡ አሳወጀ ከነመኳንንቱ
የነነዌ ሰዎች በውነት ከልቡና
መጸጸታቸውን እግዚአብሔር አየና
ፍጡር ቢለምነው እንባ እያፈሰሰ
ምሕረቱን አውርዶ መዓቱን መለሰ

**ምዕራፍ አራት**

የተናገረው ቃል ሰላልተፈጸመ
ዮናስ ተቈጥቶ እያጕረመረመ
እንደዚህ እያለ ጸለየ ወደ አምላክ
እኔን መጀመሪያ ነነዌ ለመላክ

አሰበህ ብታዘኝ ይህንኑ ዐውቄ
ወደ ተርሴስ ልሄድ ጠፋሁ ተደብቄ
ምሕረትህ የበዛ መሓሪና ታጋሽ
በደል የምትረሳ ከቊጣ ተመላሽ
የቊጣህን ያህል ምሕረትህ የጠና
መሆንክን ጥንቱንም እኔ ዐውቃለሁና
እኔን ግን ግደለኝ ልሙት ልቀበር
ሐሰት ተናግሬ የማይሆን ነገር
አልፈልግምና ቆሜ ለመኖር
ከከተማ ወጥቶ በምሥራቅ በኩል
ከወደ ዳር ሆኖ ነነዌን ሊያስተውል
ምን እንደሚያገኛት ለማየት ዮናስ
ሠርቶ ተቀመጠ አንድ ትንሽ ዳስ
እግዜር በጥበቡ አንድ ቅል አብቅሎ
ቅሉም አደገና ከፍ ከፍ ብሎ
የዮናሰ ራሱ እንዲያገኝ ጥላ
ለፀሓዩ ንዳድ ሆነለት ከለላ
በዚህ በቅል አገር ዮናስን ደስ አለው
እንዲህ ቶሎ ደርሶ ስላገለገለው
እግዜር በማግሥቱ ጧት በማለዳ
ቅል የሚበላ ትል ፈጣረ አሰናዳ
ትሉ ቅሉን በልቶ በፍጥነት ደረቀ
ፀሓይ ወጣችና ግዜው በጣም ሞቀ
እግዜር አዘዘና ትኩስ ነፋስ መጣ
የሚከለልበት መጠጊያ ስላጣ
ቅሉ ደረቀና ንዳድ ቢያቃጥለው
ዮናስ ተበሳጭቶ ላምላክ እንዲህ አለው
እንደዚህስ ሆኜ ቆሜ ከምኖር
እባክህ ግደለኝ ልሙት ልቀበር
ደረቀብኝ ብለህ ይህን ቅል ለማጣት
እውን ይገባል ወይ ያንተ አሁን መቈጣት?
ብሎ እግዜር ቢጠይቅ መለሰ ዮናስ
በንዴቱ ብዛት እስክሞት ድረስ
አዎን ይገባኛል መናደድ መጤስ
እግዜርም መለሰ ለምን ጠፋ ስትል
ይህ ያልለፋህበት ያልደከምህበት ቅል
አንተ ስትናደድ ፈጥሬአት እኔማ
ሳጠፋት ሳፈርሳት ነነዌን ከተማ
መቶ ሓያ ሺህ ነው የሕዝብዋ ብዛት
ለምን ትቈጣለህ እኔ ባዝንላት
ብሎ በምሳሌ ሲያስተምር ይቅርታ
ለዮናስ ነገረው የምሕረቱ ጌታ
ለእግዚአብሔር ቸርነት ምስጋና ይድረስ
በዚህ ተፈጸመ ትንቢተ ዮናስ።

ከክቡር አቶ ከበደ ሚካኤል የቅኔ አዝመራ (1956) ከሚለው የተወሰደ